የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፴፩
አዲስ አበባ – መጋቢት ፩ ቀን ፲፱፻፹፱

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

3rd Year No.31
ADDIS ABABA – 10th Mar. 1997

## ማውጫ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፲፮/፲፱፻፹፱ ዓ.ም.
የኢትዮጵያ የዕፅዋት ዘር የሚኒስትሮች ምክር ቤት
ደንብ ........................................................ ገጽ ፬፻፺፱

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፲፮/፲፱፻፹፱
## የኢትዮጵያ የዕፅዋት ዘር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፯ አንቀጽ ፭ መሠረት የሚከተለውን ደንብ አውጥቷል።

፩· <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ የዕፅዋት ዘር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፲፮/፲፱፻፹፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· <u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም ካልሰጠው በስተቀር በዚህ ደንብ፣

፩· "ምክር ቤት" ማለት አግባብ ያላቸው መሥሪያ ቤቶች ተወካዮች በአባልነት የሚገኙበት ሥልጣንና ተግባሩ በአዋጅ ቁጥር ፶፮/፲፱፻፹፭ ተወስኖ የተሰጠው አካል ነው ፤

፪· "ድርጅት" ማለት ብሔራዊ የዕፅዋት ዘር ኢንዱስትሪ ድርጅት ነው ፤

፫· "ዝርያ" ማለት ከሌሎች ዝርያዎች በግልጽ የሚለይበት ተወራራሽ የሆነ መለያ ጠባይ ያለው የዕፅዋት ዘር ነው ፤

## CONTENTS

Council of Ministers Regulations No. 16/1997
Ethiopian Seed Council of Ministers
Regulations ............................................ Page 499

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS NO. 16/1997
## THE ETHIOPIAN SEED COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS

These Regulations are issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 4/1995

1. *Short Title*

These Regulations may be cited as the "Ethiopian Seed Council of Ministers Regulations No. 16/1997."

2. *Definitions*

In these Regulations unless otherwise the context requires;

1) "Council" means the national Seed Industry Council composed of appropriate members from relevant organizations whose powers and duties are given under Proclamation No. 56/1993;
2) "Agency" means the national Seed Industry Agency;
3) "Variety" means subdivision of any kind of plant seed that can be differentiated from other subdivision of that kind by heritable characters;

፬· "የተመሠከረለት ዘር" ማለት በአገር ውስጥ የተመረተ ወይም ወደ አገር ውስጥ የገባ አስፈላጊዎቹን የዘር መስፈርቶች (ደንቦች) ማሟላቱን በድርጅቱ ወይም ይህንን ሥራ ለማከናወን በሕግ በተፈቀደለት ሌላ አካል የተረጋገጠለት፣ በቀጥታ ለተጠቃሚዎች ቀርቦ በዘርነት የሚውል ነው ፤

፭· "ዘር" ማለት እውን ዘር፣ አኩራች፣ ድንች፣ ቅጥፍ ተክል፣ የማሳ ሰብሎችና የጓሮ አትክልት ችግኞች፣ ወይም ለሰብል ማራባት የሚያገለግል የተክል ክፍል ወይም አካል ነው ፤

፮· "የተደነገገ ዘር" ማለት የዚህ ደንብ አንቀጾች ተፈጻሚ የሚሆንበትና ድርጅቱ በሚያወጣው መመሪያ የተወሰነ ዘር ነው ፤

፯· "አጽዳቂ ኮሚቴ" ማለት ብሔራዊ የዝርያ አጽዳቂ ኮሚቴ ነው ፤

፰· "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው ፤

፱· "የዘር መረጃ ማዕከል" ማለት የብሔራዊ ዕፅዋት ዘር ኢንዱስትሪ ድርጅት የዘር መረጃ ማዕከል ነው ፤

፲· "ንጽሕና" ማለት በመቶኛ፣ በክብደት ወይም በሌላ መንገድ የተገለጸ ትንታናዊ ንጽሕና ነው ፤

፲፩· "ውግዝ የአረም ዘር" ማለት በዚህ ደንብ ድንጋጌዎች መሠረት ተለይቶ የታወቀ ልዩ የአረም ብቸኛ ዝርያ ዘር ማለት ነው ፤

፲፪· "ምልክት" ማላት ማብራሪያ፣ ምስል ወይም ንድፍ ነው፤

፲፫· "ማስታወቂያ" ማለት በጋዜጣ፣ በስእል፣ በፖስተር፣ በቅርጽ ወይም በሌላ ሕትመቶች ሕዝቡ እንዲያ ውቀው የሚቀርብ ነው ፤

፲፬· "የዘር ማበጠሪያና ማዘጋጃ" ማለት የማይፈለጉ ነገሮችን ከዘሩ ውስጥ ለማስወገድ አስፈላጊውን የዘር አቅርቦት ዝግጅቶችን ለማድረግ የሚያገለግል የተከለለ ቦታ ነው ፤

፲፭· "ውሱን ዘር" ማለት ወደ ኢትዮጵያ እንዳይገባ ወይም ከኢትዮጵያ እንዳይወጣ የተከለከለ ወይም ገደብ የተደ ረገበት ዘር ነው።

፫· <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

፩· ይህ የዕፅዋት ዘር ደንብ ምክር ቤቱ በሚወስነው በማናቸውም የተጠቃሽ ዝርያ የተደነገገ ዘር ላይ ተፈጻ ሚነት ይኖረዋል።

፪· የዚህ ደንብ ድንጋጌዎች በአርሶ አደሩ ማሳ ላይ በተመረተ ዘርና ከአምራች አርሶ አደር ወደ ሌላ አርሶ አደር በሚሸጥ ዘር ላይ ተፈጻሚ አይሆንም። ሆኖም ግን በዘር ሽያጭ ሥራ ላይ ለመሠማራት ዘሩን በአስተዋወቀ በማንኛውም አምራች፣ አዘጋጅና አከፋፋይ ላይ የደንቡ ተፈጻሚነት የተጠበቀ ነው።

፫· ለዘር የሚውሉ ካልሆነ በስተቀር የዚህ ደንብ ድንጋጌ በሌላ ጥቅም በሚውሉ ዕፅዋቶች ተፈጻሚ አይሆንም ።

፬· <u>ዝርያዎችን ስለማጽደቅ፣ ስለመሰየምና ስለመመዝገብ</u>

የዚህ ደንብ አንቀጾች እንደተጠበቁ ሆነው የማናቸውም ተክል ብቸኛ ዝርያ አዲስ ዝርያ የሚፀድቀው፣ የሚሰየመው እና የሚመዘገበው ይህ ዝርያ አጽዳቂ ኮሚቴው ካወጣቸውና ከሚያወጣቸው ዝርዝር ሁኔታዎች ጋር ሲጣጣም ብቻ ነው።

፭· <u>ስለ ምዝገባና ሥራ ፈቃድ</u>

፩· ድርጅቱ የተደነገገ ዘር አምራቾች፣ አዘጋጆች፣ አከፋፋ ዮችና ሻጮች የሚመዘገቡበትን መመሪያ ያወጣል።

4) "Certified Seed" means a seed produced in Ethiopia or imported seed that has been certified by the Agency or other body authorized to do this to conform to the standards established and that is intended for production;

5) "Seed" means true seed, bulbs, tubers, cuttings, nursery plants of field and garden crops or any other plant material used for the propagation of plants;

6) "Prescribed Seed" means any seed to which provisions of this Regulations and Directive to be issued by the Agency are applicable;

7) "Release Committee" means the National Variety Release Committee;

8) "Person" means a natural person or juridical body;

9) "Seed Data Base" means the Seed Data Base of the National Seed Industry Agency;

10) "Purity" means analytical purity expressed as a percentage, weight or other means;

11) "Objectionable Weed Seeds" means seeds of a specific weed species identified as such and is subject to the provisions of these Regulations;

12) "Label" means any legend, symbol or design;

13) "Advertisement" means any statement, picture, design or device published in any newspaper or other publications and brought to the notice of the public;

14) "Seed Processing Plant" means any premises used for seed processing (cleaning, grading, treating, bagging and labelling);

15) "Restricted Seed" means seed prohibited from being imported into Ethiopia or exported from Ethiopia or seed put under resetriction.

3. *Scope of Application*

1) These Regulations shall apply to any prescribed seeds of any designated variety of any plant species as may be specified by the Council.

2) The provisions of this Regulations shall not apply to a seed produced by a farmer on his own field and sold directly to another farmer. However, these Regulations shall apply on any producer, processor and distributor who advertised his seed to participate on a sale of seeds.

3) Unless used for seed, provisions of these Regulations shall not apply to seeds of plants intended for other purposes.

4. *Naming, Approval and Registration of Varieties*

A new variety of any plant species subject to the provisions of these Regulations shall be approved, named and registered only when such a variety conforms to the terms and conditions prescribed by the Release Committee.

5. *Registration and Work Permit*

1) The Agency shall issue Directives under which producers, importers, processors, distributors or sellers of a prescribed seed are registered.

፪· በድርጅቱ ካልተመዘገበ በስተቀር ማናቸውም ሰው የተደነገገ ዘር ማምረት ፣ ማስመጣት ፣ ማዘጋጀት ፣ ማከፋፈልና የሽያጭ ንግድ ሥራ ላይ መሰማራት አይቻልም።

፫· የተደነገገ ዘር አምራች፣ አስመጪ፣ አዘጋጅ፣ አከፋፋይና ሻጭ ሆኖ ለመመዝገብ ለድርጅቱ የሚቀርብ ማመልከቻ ለሚሰጠው አገልግሎት የሚከፈለውን ክፍያ ጨምሮ በተወሰነው መሠረት ይሆናል።

፬· አመልካቹ በዚህ ደንብ አንቀጾች የተጠቀሱትንና ሌሎች ግዴታዎችን ማክበሩን ለማረጋገጥ ድርጅቱ እንደአስፈላጊነቱ በምዝገባ ወቅት በማናቸውም የተደነገገ ዘር አምራች፣ አስመጪ፣ አዘጋጅ፣ አከፋፋይ ወይም ሻጭ ላይ የተለየ ሁኔታንና ገደብን ሊጥል ይችላል። እንዲሁም የተወሰነ ዝርያ የሚዘራበትን የመሬት ስፋት፣ በአመልካቹ የሚመረቱትን ዝርያዎች፣ ወቅቱን፣ ክልሉን የቦታውን የመገለል አስፈላጊነት፣ ወይም ሌሎች ሁኔታዎች መወሰንን ይጨምራል።

፭· በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚደረገው ምዝገባ በደንቡ አንቀጾች መሠረት እስኪሰረዝ ድረስ ፀንቶ የሚቆይ ሲሆን ክፍያው በተወሰነ መሠረት በየዓመቱ ተግባራዊ ይሆናል።

፮· የምዝገባው ማብቂያ ዘመን ከመድረሱ በፊት ድርጅቱ በቂ በሆነ ምክንያት ሊሠርዝ ወይም በማናቸውም ነገር ላይ ለውጦችን ማድረግ የሚችል ሲሆን በዚህም ጉዳይ ላይ የሚከተሉት ንዑስ አንቀጾች ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል።

ሀ) ድርጅቱ ምዝገባውን ለመሠረዝ ወይም ለውጦች ለማድረግ መፈለጉን ከበቂ ምክንያት ጋር በመግለጽ የአሥራ አራት ቀን የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በጽሑፍ ለተመዘገበው ሰው ካልሰጠ በስተቀር ምዝገባውን ሊሠርዝ ወይም ለውጦች ሊያደርግ አይችልም።

ለ) የተደረጉ ለውጦችን ወይም ስረዛን አስመልክቶ የተመዘገበው ሰው በዚህ አንቀጽ (ሀ) መሠረት ለደረሰው ማስጠንቀቂያ ቅሬታውን ለድርጅቱ ከገለጸ ድርጅቱ ቅሬታው እንደደረሰው በአሥራ አራት ቀናት ውስጥ ውሳኔውን ለተመዘገበው ሰው በጽሁፍ መስጠት ይኖርበታል።

፯· የተደነገገ ዘር አምራች፣ አስመጭ፣ አዘጋጅ፣ አከፋፋይና ሻጭ ሆኖ ለመመዝገብ የቀረበ ማመልከቻ ተቀባይነት ማጣት ድርጅቱን በሚያጠግብ ሁኔታ አስፈላጊውን እርማት አድርጎ በሚቀጥለው ጊዜ ለምዝገባ አዲስ ማመልከቻ ለማቅረብ አመልካቹን አያግደውም።

፰· የተደነገገ ዘር አምራች፣ አስመጭ፣ አዘጋጅ፣አከፋፋይና ሻጭ ለመሆን የምዝገባ ማመልከቻ ለመቀበል ሲባል ድርጅቱ ወይም እሱ የወከለው ባለሥልጣን በማና ቸውም ተስማሚ በሆነ ጊዜ አመልካቹ ለማምረትና ለንግድ የሚጠቀምበትን ቦታ፣ መጋዘን፣ ማከማቻ እና ሌሎች ነገሮችን ተገኝቶ መመርመር ይችላል።

፮· __መረጃ ስለመያዝ__

ማንኛውም የተመዘገበ የተደነገገ ዘር አምራች፣ አስመጭ፣ አዘጋጅ፣ አከፋፋይ እና ሻጭ ፤

፩· እያንዳንዱን ማሣ፣ ያመረተውን ዘር፣ ወደ ሀገር ውስጥ ያስገባውን፣ ያዘጋጀውን፣ የገዛውና የሸጠውን ዘር በዝርዝር መዝግቦ ይይዛል።

፪· ትንተና የተካሄደባቸውን የተክል ናሙናዎች ይይዛል።

2) No person shall engage in the business of production, importation, processing, distribution or sale of any prescribed seed unless he has been registered by the Agency.

3) An application for registration as a producer, importer, processor, distributor or seller of a prescribed seed shall be made to the Agency in the prescribed manner and shall be accompanied with such fees as may be prescriibed.

4) The Agency may impose such conditions and limitations upon registration of any producer, importer, processor, distributor or seller of a prescribed seed as may be deemed necessary including limitations as to the hectarage to be cultivated under specified variety or varieties to be produced by such applicant or season, region or special isolation requirements or otherwise, to ensure that the applicant complies with the provisions of these Regulations or with any prescribed requirements.

5) A registration under this Article shall be valid until canceled under the provisions of these Regulations but shall be subject to payment of such fees as may be prescribed to be payable annually.

6) The Agency, for good cause to do so, may cancel the registration or make any alterations in any respect before the expiry date of registration and in such cases the following provisions apply:

(a) the Agency shall not make any such cancellation or alterations unless he has given to the registered person at least fourteen days notice in writing that the Agency is considering making the cancellation or alteration and shall state the grounds for doing so.

(b) the Agency shall consider any grievance in relation to such alteration and cancellations made to it by the person to whom notice under (a) was given and shall give to the person its decision in writing within 14 days.

7) A refusal of an application for registration as a producer, importer, processor, distributor or seller of a prescribed seed shall not preclude the applicant from making a fresh application for registration at any subsequent time provided the necessary corrections are made to the satisfaction of the Agency.

8) For the purpose of considering an application for registration as a producer, importer, processor, distributor or seller of a prescribed seed the Agency or any authority appointed by it may at any reasonable time inspect the field, warehousing, storage, and other facilities which the applicant proposes to use in and about his business.

6. *Keeping Records*

Any registered producer, importer, processor, distributor or seller of a prescribed seed shall:

1) record and keep particulars of each field, seed produced, imported, processed, purchased and sold;

2) keep records of seed samples on which analyses have been made.

፫· ከላይ በንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) መሠረት የያዘውን መረጃ በተጠየቀ ጊዜ ለድርጅቱ የዘር መረጃ ማዕከል ወይም ኢንስፔክተር ለቁጥጥር ያቀርባል ።

፯· <u>ስለጥራት ቁጥጥር</u>

፩· የኢትዮጵያ ደረጃዎች መዳቢ ባለስልጣን የማንኛውንም ተጠቃሽ ዝርያ ዘር የጥራት ደረጃ ይወስናል። ለዚህ ደንብ ሲባል ድርጅቱ የተወሰነውን የጥራት ደረጃ ተግባራዊ ያደርጋል።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በዘር መርማሪው አማካኝነት ምርመራ ተካሂዶ ማናቸውም የተደነገገ ዘር ከተወሰነው የጥራት ደረጃ ጋር የማይጣጣም ሆኖ ሪፖርት የተደረገ ከሆነ ባለቤቱ ወዲያውኑ የተደነገገው ዘር እንዲታከም ወይም እንዲጸዳ ማድረግ ይኖርበታል።

፫· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪)መሰረት ማናቸውም የተደነገገ ዘር ከታከመ ወይም ከጸዳ ባለቤቱ የዘር ተቆጣጣሪውን የዘሩን ናሙና ለተጨማሪ ምርመራ ወደ ምርመራው ማዕከል እንዲልክ ሊጠይቀው ይችላል። የተደነገገው ዘር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት ከተወሰነው የጥራት ደረጃ ጋር መጣጣሙን የዘር መርማሪው ሪፖርት እስከሚያደርግ ድረስ ባለቤቱ የተደነገገውን ዘር በተጨማሪ ማሳከም ወይም ማጽዳት ይኖርበታል።

፬· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫)መሠረት ለሚደረገው ተደጋጋሚ የዘር ምርመራ ባለቤቱ ለእያንዳንዱ ለሚደረገው ምርመራ የተወሰነውን ክፍያ ይከፍላል።

፰· <u>መለያ ምልክት ስለማድረግ</u>

የዚህ ደንብ አንቀጾች እንደተጠበቁ ሆነው በአንቀጽ ፯ መሠረት የተመረመረ ማናቸውም የተደነገገ ዘርን የሚሸጥና በአንቀጽ ፱ ላይ የተገለጹትን ሁኔታዎች የሚያሟላ ማናቸውም የተመዘገበ የዘር ሻጭ ከታች የተዘረዘሩትን ተግባሮች የመፈጸም ግዴታ አለበት።

፩· የሚሸጠው የተደነገገ ዘር በታሸገ መያዣ ከሆነ፣

ሀ) የአምራቹ ኩባንያ ስምና አርማ፣

ለ) እንደሁኔታው "የተመሰከረለት ዘር" ወይም "ወደ አገር ውስጥ የገባ የተመሰከረለት ዘር" የሚል ቃል፣

ሐ) የተደነገገው ዘር የተመረመረበት ቀንና ዓመተ ምህረት ፣ እና

መ) ሌሎች የተወሰኑ ዝርዝሮችን መያዣው ላይ እንዲታተም ወይም በተወሰነ መለያ ምልክት ላይ ተጽፈው እንዲለጠፉ ያደርጋል።

፪· የተደነገገው ዘር በብዛት የሚሸጥ ከሆነ፣

ሀ) ምርመራው እንዲከናወን ያደረገው እራሱ ሻጩ ከሆነ ሽያጩ በሚፈጸምበት ጊዜ ምርመራ የተካሄደበትን ማዕከል ስምና አድራሻ፣ ምርመራ የተካሄደበትን ቀንና ዓ.ም፣ ምርመራው ሲከናወን የተወሰደው ናሙና ከተሸጠው ዘር በከፊል ወይም በሙሉ መሆንና ሌሎች ዝርዝሮችን የያዘ ዝርዝር መግለጫ በጽሑፍ ለገዢው ያቀርባል።

3) provide such record kept above under sub-Articles (1) and (2) when requested for the Agency's Seed Data Base or Inspector for control.

7. *Quality Control*

1) The Ethiopian Authority for Standardization shall prescribe quality standards with respect to a prescribed seed of a designated variety and the Agency shall adopt the quality standards for the purpose of these Regulations.

2) If upon test made under sub Artile (1) of this Article, it is found and reported by an Official Seed-Tester that any prescribed seed does not conform to the prescribed quality standards, the owner thereof shall forthwith arrange for the prescribed seed to be treated or cleaned.

3) Where any prescribed seed has been treated or cleaned pursuant to sub-Article (2) of this Article the owner may request a Seed-Inspector a further sample to be sent to a Seed-Testing Station for further test. The owner may, as often as he so desires, cause further treatments or processing of such prescribed seed to be effected and further tests to be made in like manner until such time as the prescribed seed is found and reported by the Official Seed-Tester to conform to quality standards prescribed in sub-Article (1) of this Article.

4) In such cases as the owner causes repeated testing of such a seed as prescribed in sub Article (3) of this Article, the owner shall pay such fees as may be prescribed for each test.

8. *Labelling*

Subject to the provisions of these Regulations, any registered seed seller who sells any prescribed seed which has been tested in accordance with the provisions of Article 7 and found to comply with the provisions of Article 9 shall do the following:

1) If the prescribed seed to be sold is in a sealed container, the seller would cause:

(a) the name of the company and its emblem,

(b) the words "Certified Seed" or "Imported Certified Seed" as the case may be,

(c) the date upon which the prescribed seed was tested, and

(d) other specified particulars to be printed or stamped upon such container or upon a specified label attached there to or enclosed therein.

2) If the prescribed seed is sold in bulk quantities:

(a) and the seller is the person who caused the test to be made, furnish to the buyer at the time of sale a statement in writing containing the name and address of the seed-testing station where the test was made, the date of the test, a declaration that the bulk quantity sold is all or part of that from which the sample tested was taken and such other particulars.

ለ) ምርመራው እንዲከናወን ያደረገው ሻጩ ካልሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ (ሀ) መሠረት ምርመራውን እንዲካሄድ ያደረገው ሰው ያዘጋጀውን መግለጫ ግልባጭ እንዲሁም መግለጫው የተሸጠውን ዘር በሙሉ ወይም በከፊል ይሸፍን እንደሆነ ማረጋገጫ ለገዥው ይሰጣል።

፱· <u>የዘር ሽያጭን ስለመቆጣጠር</u>

፩· ማናቸውም ሰው በሥራ ፈቃድ ላይ በተዘረዘሩት ሁኔታዎች መሠረት የሚዘራ የተደነገገ ዘር ለመሸጥ የሚያስችል የዘር ሻጭ የሥራ ፈቃድ ካልኖረው በስተቀር ማናቸውንም የተደነገገ ዘር ለመሸጥ አይችልም ።

፪· አመልካቹ የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች ወይም በደንቡ መሠረት የሚወጡትን ማናቸውንም አስፈላጊ ነገሮች ማክበሩን ለማረጋገጥ ድርጅቱ እንደአስፈላጊነቱ የሥራ ፈቃድ መስጠትን በተመለከተ የተለያዩ ሁኔታዎችን ሊያስቀምጥ ይችላል።

፫· ማንም ሰው ማንኛውንም የተደነገገ ዘር ለመሸጥ፣ ለሺያጭ ለማስቀመጥ፣ ለሺያጭ ለማቅረብ፣ በዓይነት ለመለወጥ፣ ወይም በሌላ አኳኋን ለማቅረብ የሚችለው፤

ሀ) የተባለው ዘር የተጠቃሹ ዝርያ ለመሆኑ ሲረጋገጥ፣

ለ) በዚህ ደንብ በተወሰነው መሠረት የተወሰደው የዘሩ ናሙና በታወቀ የዘር መመርመሪያ ጣቢያ የተመረመረ ሲሆን፣

ሐ) ዘሩ በአንቀጽ ፯ ከተገለጸው የዘር የጥራት ደረጃ ማለትም ከመብቀልና ከንጽህና ዝቅተኛ ገደብና እንዲሁም ከእርጥበቱና ከውጉዝ የአረም ዘር ከፍተኛ መጠን ጋር ተጣጥሞ ሲገኝ፣

መ) መያዣው በአንቀጽ ፰ በተደነገገው መሠረት ይዘቱ ግልጽ በሆነና በተወሰነው መሠረት ምልክት የተደረገበት ሲሆን ።

፲· <u>ዘርን ስለማረጋገጥ</u>

የዚህ ደንብ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፤

፩· በኢትዮጵያ ውስጥ የተመረተ ዘር ከሆነ የተመሰከረለት ዘር መሆኑ ፣ ወይም

፪· ወደ ሀገር ውስጥ የገባ ዘር ከሆነ፤ ወደ ሀገር ውስጥ የገባ የተመሰከረለት ዘር መሆኑብድርጅቱ ወይም ይኽን ሥራ ለመሥራት በተፈቀደለት ሌላ አካል መረጋገጥ አለበት።

፲፩· <u>የውጭ ሀገር የዘር አረጋጋጭ ድርጅቶችን እውቅና ስለመስጠት</u>

ለዚህ ደንብ አፈጻጸም ሲባል ድርጅቱ ውጭ ሀገር ለተቋቋሙ ማናቸውም የዘር አረጋጋጭ ድርጅቶች እውቅና ሊሰጥ ይችላል።

፲፪· <u>የምስክር ወረቀት ስለመስጠት</u>

፩· ማናቸውንም የተጠቃሽ ዝርያን የተደነገገ ዘር የሚሸጥ፣ ለሽያጭ የሚያስቀምጥ፣ ለሽያጭ የሚያቀርብ፣ የሚለውጥ ወይም በሌላ አኳኋን የሚያቀርብ ሰው ፤

ሀ) የተባለውን ዘር የምስክር ወረቀት እንዲኖረው ፍላጎት ካለው የምስክር ወረቀቱን ለማግኘት ለድርጅቱ ማመልከት ይኖርበታል ፤

ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ (ሀ) መሠረት የሚቀርበው ማመልከቻ ከተወሰነው ክፍያ ጋር በዝርዝር በተገለጸው መሠረት መቅረብ ይኖር በታል።

፪· የምስክር ወረቀት አሰጣጥ በሚከተለው ሁኔታ ይፈጸማል፤

(b) and the seller is not the person who caused the test to be made, furnish to the buyer at the time of sale a copy of the statement furnished under the provisions of sub Article 2(a) of this Article and shall endorse thereon a declaration that the bulk quantity sold by him is all or part of the seed sold.

9. *Control of Sale of Seeds*

1) No person shall sell any prescribed seed unless he has a seed seller's work permit issued to sell for sowing a prescribed seed in accordance with the terms and conditions of the work permit.

2) The Agency may impose such conditions with regard to the issuance of the work permit as it may deem to be necessary in order to insure that the applicant complies with the provisions of these Regulations.

3) Any person can sell, keep for sale, offer for sale, exchange in kind or supply through other means if only:

(a) such seed is identifiable to its designated variety;

(b) a sample of the seeds, taken in the prescribed manner, has been tested at an official seed testing station;

(c) such seed conforms to the minimum limits or tolerance levels of germination and purity and maximum levels of moisture content and total and/or objectionable weed seeds specified under Article 7; and

(d) the container is distinctly marked in prescribed manner to reflect that the contents conform with the provisions of Article 8.

10. *Seed Certification*

Subject to the provisions of these Regulations, seed shall be certified by the Agency or other authorized body as follows:

1) In the case of seed produced in Ethiopia as "Certified Seed" or

2) in the case of imported seed as "Imported Certified Seed."

11. *Recognition of Certification Agencies of Foreign Countries*

The Agency may recognize any certification agencies established in any foreign country for the purpose of these Regulations.

12. *Issuance of Certificate*

1) A person who sells, keeps for sale, offer for sale, exchange in kind or supply through other means any prescribed seed of any designated variety:

(a) if he desires to have such seed certified, apply to the Agency or other authorized body to do this for the issuance of a certificate.

(b) an application made under sub Article (1) (a) of this Article shall be made in the prescribed manner and shall be accompanied with such fees as may be prescribed.

2) Issuance of certificate shall be carried out in the following manner:

ሀ) በኢትዮጵያ ውስጥ የተመረተ የተደነገገ ዘርን በተመለከተ ፤
  ፩· በቅርብ ጊዜ በተዘጋጀ የዝርያ ዝርዝር ውስጥ የተመዘገበ ዝርያ መሆኑን ፤
  ፪· የምስክር ወረቀት ከሚሰጣቸው ደረጃዎች ውስጥ መሆኑን ፤
  ፫· በተመዘገበ የዘር አምራች የተመረተ መሆኑን ፤
  ፬· በተወሰነው መሠረት መመረቱን ፤
  ፭· በተወሰነው መሠረት በእርሻ ወቅት ቁጥጥር የተደረገበት መሆኑን ፤
  ፮· በዚህ ደንብ ድንጋጌዎች መሠረት የተመረመረ መሆኑንና ከአስፈላጊዎቹ የጥራት ደረጃዎች ማለትም ከመብቀልና ከንጽህና ዝቅተኛ ገደብ፣ ከእርጥበት ከፍተኛ መጠን ጋር የተጣጣመና እንዲሁም የተደነገገ ተጠቃሽ ዝርያን አስመልክቶ የተገለጸውን የዘር አረም ያስወገደ መሆኑን አመልካቹ ለድርጅቱ ያሳያል።

ለ) ወደ ኢትዮጵያ የገባ የተለየ የተደነገገ ዘርን በተመለከተ ፤
  ፩· በተመዘገበ የዘር አስመጪ ወደ ኢትዮጵያ የገባ መሆኑን ፤
  ፪· በዚህ ደንብ አንቀጽ ፯ እና ፰ ድንጋጌዎች መሠረት የተመረመረ መሆኑን ፤
  ፫· ዘሩ ከመጣበት ሀገር ሕግ መሠረት የተመሰከረለት ዘር ተብሎ የተረጋገጠ ሲሆን ፤
  ፬· በዚህ ደንብ መሠረት የተመሰከረለት ዘር የሚመረትበትን ደረጃ በመብለጥ ወይም እኩል በመሆን የተመረተ መሆኑን ፤
  ፭· በዕፅዋት ኳራንቲን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፭ የተደነገጉ የኳራንቲን መስፈርቶችን ያሟላ መሆኑን ፤
  ፮· በዚህ ደንብ አንቀጽ ፬ የተደነገገውን ያሟላ መሆኑን አመልካቹ ለድርጅቱ ያሳያል።

ሐ) ድርጅቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ (ሀ) እና (ለ) ስር የተዘረዘሩት ሁኔታዎች በአጥጋቢ ሁኔታ መሟላታቸውን ካረጋገጠ በኋላ በወሰነው ሁኔታ እና በአዘጋጀው ፎርም እንደሁኔታው ዘሩ ሀገር ውስጥ የተመረተ የተመሠከረለት ዘር ወይም ወደ ሀገር ውስጥ የገባ የተመሠከረለት ዘር ነው በማለት ሊያረጋግጥ ይችላል።

መ) ድርጅቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪(ሀ) እና (ለ) መሠረት ማንኛውም ዘር የተመሰከረለት ዘር ነው በማለት ካረጋገጠ በኋላ እንደሁኔታው የምስክር ወረቀት በተወሰነው ፎርምና ሁኔታ ለተመዘገበ አምራች ወይም አስመጭ ይሰጣል።

፲፫· ምሥክር ወረቀትን ስለመሰረዝ

፩· ድርጅቱ በዚህ ደንብ መሠረት የሰጠውን የምሥክር ወረቀት የሚሰርዘው ፤
  ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፪ መሠረት የተሰጠው የምሥክር ወረቀት አስፈላጊ ሁኔታዎችን በተመለከተ የማጭበርበር ተግባር በመፈጸም የተገኘ ሲሆን ፤ ወይም
  ለ) የምሥክር ወረቀቱ ባለቤት የምሥክር ወረቀቱን ለማግኘት ሲል የገባውን ግዴታ ያለበቂ ምክንያት ያላሟላ ከሆነና የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች ወይም በዚህ ደንብ መሠረት የወጡ መመሪያዎችን ጥሶ ሲገኝ ይሆናል።

(a) Regarding prescribed seed produced in Ethiopia, an applicant shows to the Agency or other authorized body to certify that his seed:
  1) is of a specified variety in the current Variety List;
  2) is of a known certification class;
  3) has been produced by a registered seed producer;
  4) has been produced as priscribed;
  5) has been inspected during cultivation as prescribed; and
  6) has been tested in accordance with the provisions of these Regulations and found to conform to the minimum limits or tolerance levels of germination and purity, and maximum limits of moisture content and total and/or objectionable weed seed.

b) Regarding particular prescribed seed imported into Ethiopia, an applicant shows to the Agency or other authorized body to certify that his seed:
  1) is imported into Ethiopia by a registered seed importer;
  2) is tested in accordance with the provisions of Article 7 and 8 of these Regulations;
  3) is certified as "Certified Seed" under the current laws of the country of its origin;
  4) is produced under conditions conforming to the standards equal to or higher than those prescribed for the production and certification of "Certified Seed";
  5) complies with the provisions of plant quarantine regulations on importation of seeds, Council of ministers Regulation No. 4/1992;
  6) complies with the provisions of Article 4 of these Regulations the Agency may certify such seed as "Imported Certified Seed" in such form and on such conditions as may be prescribed.

(c) The Agency or other authorized body for certification, after insuring that conditions enumerated under this Article sub-Articles 2(a) and (b) have been satisfactorily fulfilled, may certify such seed is "Certified Seed" or Imported Certified Seed as the case may be in such form and on such conditions as may be prescribed.

(d) Having certified any seed as " Certified Seed" or "Imported Certified Seed" on the basis of this Article, sub-Articles 2(a) and (b), the Agency shall issue to the registered producer or importer as the case may be, a certificate in such form and on such conditions as may be prescribed.

13. *Revocation of Certificate*

1) The Agency may revoke the certificate issued under these Regulations if:
  (a) The certificate issued by it under Article 12 has been obtained by misrepresentation as to essential conditions; or
  (b) The holder of the certificate has, without reasonable cause, failed to comply with the conditions subject to which the certificate has been issued or has contravened any of the provisions of these Regulations or the Directives thereunder.

፪· ድርጅቱ የምሥክር ወረቀቱን ከመሠረዙ በፊት ለባለቤቱ ጉዳዩን የማስረዳት ዕድል ሊሠጥ ይችላል።

፫· ከላይ የተደነገገው ባይኖርም የድርጊቱ ፈጻሚ አግባብ ባለው የወንጀል ድንጋጌ መጠየቁ የተጠበቀ ነው።

፲፬· <u>የዘር ምርመራ ማዕከላትን ስለማቋቋም፣ ለተቋቋሙት ዕውቅና ስለመስጠትና የዘር ተንታኞች ስለመመደብ</u>

፩· ድርጅቱ ከምክር ቤቱ ጋር በመመካከር በተወሰነው መሠረት የተደነገገ ዘር ምርመራ የሚከናወንባቸውን የዘር ምርመራ ማዕከላትን ያቋቁማል፣ የተቋቋሙትን እና/ወይም የሚቋቋሙትን ያውቃል ።

፪· በተወሰኑት ሁኔታዎች መሠረት የዘር ምርመራ እንዲከናወን የዘር ተንታኞች ይመድባል።

፲፭· <u>የዘር ናሙና ስለመውሰድና ትንተና ስለማካሄድ</u>

፩· ጥራቱ ያልተመረመረ የተደነገገ ዘር ያመረተ ወይም የያዘ ማናቸውም ሰው ዘሩን ለመሸጥ ከፈለገ ከመሸጡ በፊት በዚህ ደንብ በተወሰነው መሠረት የዘሩን ናሙና በድርጅቱ ለተቋቋመ ወይም ዕውቅና ላገኘ ለዘር ምርመራ ማዕከል ያቀርባል።

፪· ከላይ እንደተመለከተው የዘር ናሙና ለምርመራ የሚያቀርብ ሰው ዘሩ ከየት እንደመጣ ዓይነቱንና ድርጅቱ በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰኑ ሌሎች ዝርዝሮችን ያካተተ መግለጫ ማቅረብ አለበት።

፫· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)መሠረት ለሚደረገው የተደነገገ ዘር ናሙና ምርመራ አስመርማሪው የተወሰነውን ክፍያ የመክፈል ግዴታ አለበት።

፬· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)መሠረት የተወሰደው ናሙና በዘር ምርመራ ማዕከል እንደደረሰ የተመደበው የዘር ተንታኝ የተወሰነውን ሥርዓት በመከተል በናሙናው ላይ ምርመራ አካሂዶበት ምርመራው እንዲካሄድለትና የምርመራው ውጤት እንዲደርሰው ለፈለገው ሰው የምርመራውን ውጤትና ለሪፖርቱ አስፈላጊ ናቸው የሚላቸውን ሌሎች ዝርዝሮች በመግለጫ ይሰጣል።

፲፮· <u>ስለዘር ኢንስፔክሽን</u>

፩· ለዚህ ደንብ አፈጻጸም ሲባል ድርጅቱ የዘር ኢንስፔክተር ይመድባል።

፪· ድርጅቱ ለእያንዳንዱ የዘር ኢንስፔክተር የመቆጣጠር ሥልጣን እንዳለው የሚያሳይ የምስክር ወረቀት ይሰጣል።

፫· የዘር ኢንስፔክተሩ በዚህ ደንብ በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ሥራውን በሚያከናውንበት ወቅት ቁጥጥሩ የሚካሄድበት ማናቸውም ሰው በጠየቀ ጊዜ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(፪) የተመለከተውን የምስክር ወረቀት ማሳየት አለበት።

፬· <u>የዘር ኢንስፔክተሩ፤</u>

ሀ) ዘሩ የተጠቃሽ ዝርያ የተደነገገ ዘር መሆኑን ለመወሰን እንዲቻል፣

ለ) ተጠቃሹ ዝርያ የተመረተው ከተወሰነው ደረጃ ጋር በተጣጣመ መልኩ መሆኑን፣

ሐ) የተደነገገው ዘር በዚህ ደንብ መሠረት ከተወሰነው የጥራት ደረጃ ጋር የተጣጣመ መሆኑን ለማረጋገጥ ይችል ዘንድ ምርመራ ለማካሄድ ፣ እና

መ) በዚህ ደንብ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት አስፈላጊ ነው ብሎ ላመነባቸው ለሌሎች ምክንያቶች ሁሉ የዘር ወይም የተክል ናሙናዎች ሊወስድ ይችላል።

2) The Agency, before revoking the certificate, may give the holder of a certificate an opportunity of cause.

3) Even in the absence of this Article the offender's being liable under appropriate criminal code is respected.

14. *Establishing and/or Recognizing Seed Testing Stations and Apointing Seed Analysts*

1) The Agency, in consultation with the Council, shall establish and/or recognize seed testing stations in Ethiopia where testing of a prescribed seed shall be carried out in a prescribed manner.

2) The Agency shall appoint Seed Analysts to perform seed testing in accordance with the, terms and conditions as may be prescribed.

15. *Sampling and Analyses for Seed Testing*

1) Any person who has produced or acquired any prescribed seed which has not been tested for quality tests and intends to sell such seed, before selling, should take a sample thereof in the manner prescribed and deliver the sample to a seed testing station established or recognized by the Agency.

2) As indicated above, a person who delivers seed samples for testing should include ( as may be prscribed by the Agency) particulars such as the origin, type, etc.

3) The testing of a sample of prescribed seed pursuant to sub Article (1) of this Article shall be subject to such payment of fees as may be prescribed.

4) Upon receipt, at the seed testing station, of any sample taken pursuant tosub-Article (1) of this Article, the official seed-analyst shall analyze the sample in a prescribed procedure and provide the person who sought the test with the report thereof, the findings resultant therein and such other particulars as may appear to the official seed analyst necessary for or relevant to the report.

16. *Seed Inspection*

1) The Agency shall appoint a Seed Inspector for the purpose of these Regulations.

2) The Agency shall issue a certificate of authority to inspect to each seed inspector.

3) A seed inspector shall produce his certificate of authority given under thisArticle sub-Article (2) upon the demand of any person affected by the inspector exercising any of his powers under these Regualations.

4) A Seed Inspector may take samples of any seed or plant in a prescribed manner for any of the following purposes:

(a) to determine whether the seed is a prescribed seed of a designated variety;

(b) to determine if the designated variety is cultivated in conformation with the prescribed standard;

(c) to determine if the prescribed seed conforms to the quality standards prescribed under these Regulations;

(d) for such other purposes as may be deemed necessary by the inspector in relation to his powers under these Regulations;

፭· የዘር ኢንስፔክተሩ ደንቡን ለማስፈጸም ሲባል በማናቸውም ተገቢ በሆነ ሰዓት ይህንን ደንብ በመጣስ የተደነገገ ዘር ንግድ ይካሄድበታል ብሎ በሚያምንበት በማናቸውም መሬት፣ ሕንፃ፣ መኪና እና የዘር ማበጠሪያ ውስጥ በመግባት ቁጥጥር አድርጎ ንግዱን ለማካሄድ የሚያስችለውን ፈቃድ ይዞ ማቆየት ይችላል።

፮· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ፈቃዱን ይዞ ያቆየ የዘር ኢንስፔክተር ፈቃዱ ለተያዘበት ሰው ፈቃዱ መያዙን የሚገልጽና ፊርማው ያለበትን ደረሰኝ ይሰጠዋል።

፯· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) ላይ እንደተመለከተው ኢንስፔክተሩ ፈቃዱን ይዞ ካቆየ በኋላ በአሥራ አምስት ቀን ጊዜ ውስጥ አግባብ ላለው ፍርድ ቤት ጉዳዩን ማቅረብ ይኖርበታል።

፲፯· <u>ዘር ከውጭ ስለማስገባትና ወደውጭ ስለመላክ</u>

፩· የተመዘገበ የዘር አስመጪ ወይም ላኪ ካልሆነ በስተቀር ማናቸውም ሰው የተደነገገ ዘርን ለሽያጭ ወደ ኢትዮጵያ ለማስገባት ወይም ከኢትዮጵያ ወደ ውጭ ለመላክ አይችልም።

፪· ማንኛውም የተመዘገበ የዘር አስመጪ ወይም ላኪ የተደነገገ ዘርን ወደ ኢትዮጵያ ለማስገባት ወይም ከኢትዮጵያ ወደ ውጭ ለመላክ የሚችለው፤

ሀ) ዘሩ ውስን ዘር ያልሆነ ሲሆን፣

ለ) ዘሩ ከመብቀል ዝቅተኛ የጥራት ደረጃ ፣ ንጽህናና የእርጥበት ከፍተኛ መጠን ጋር የተጣጣመና ወይም የተደነገገ ተጠቃሽ ዝርያን አስመልክቶ የተገለጸን ውጉዝ የዘር አረም ያስወገደ ሲሆን፣

ሐ) በዚህ ደንብ ድንጋጌዎች መሠረት ዘሩ መለያ ምልክት የተደረገለትና በመያዣ የታሸገ ሲሆን፣

መ) በዕፅዋት ኳራንቲን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፭ የተደነገጉትን የኳራንቲን መስፈርቶች አሙዋልቶ ሲገኝ፣

ሠ) ዘሩ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፬ መሠረት ከፀደቀ፣ ከተሰየመና ከተመዘገበ ዝርያ የተገኘ ሲሆን ፣ እና

ረ) የዝርያው ስም ከመጣበት አገር የዝርያ መዝገብ ውስጥ የተመዘገበና በማስረከቢያ ቅጽ ወይም በሌላ ሰነድ ላይ የተገለጸ ሆኖ ሲገኝ ነው።

፫· ዘሩን በአስቸኳይ ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት ከመፈለግ የተነሳ የዘሩን የምስክር ወረቀት ከመጣበት ሀገር መቀበል ካልተቻለ ወይም ወደ ኢትዮጵያ የሚገባው ዘር ለምርምር ተግባር የሚውል ከሆነ ወይም በምክር ቤቱ በሚወሰኑ ሌሎች ሁኔታዎች ምክንያት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪(ረ) ላይ ከተገለጹት ሁኔታዎች ምክር ቤቱ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባን የተደነገገ ዘር ነፃ ሊያደርግ ይችላል።

፲፰· <u>ይግባኝ ስለማቅረብ</u>

፩· በዚህ ደንብ አንቀጽ ፬፣፭፣፲፪፣፲፫፣ መሠረት ድርጅቱ በሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ የተሰማው ማንኛውም ሰው ውሳኔው በደረሰው በ፴ ቀናት ውስጥ ሊኖር የሚገባውን ክፍያ በመክፈል ለምክር ቤቱ ወይም እሱ ለመደበው ባለሥልጣን ይግባኝ ማቅረብ ይችላል።

፪· ይግባኝ ሰሚው ባለሥልጣን ይግባኝ ባዩ በጊዜው ይግባኙን ማቅረብ ያልቻለው በበቂ ምክንያት መሆኑን ከተረዳ የይግባኝ ጊዜ ገደብ ፴ ቀን ቢያልፍም ይግባኙን ተቀብሎ ማየት ይችላል።

5) A Seed Inspector may, for the purposes of Execution of these Regulation at any reasonable time enter upon any land, building, vehicle, or seed processing plant which he has reasonable cause to believe is being used in the business of prescribed seed in contravention of these Regulation and inspect the same, may seize and detain the license offered to run the business.

6) A Seed Inspector who has seized and detained the license pursuant to the authority under sub-Article (5 of this Article shall give to the person from whom such license was seized a receipt with seizure's explanaiton and inspector's signature.

7) The inspector after detaining such a license as indicated in sub Article (5) of this Article shall bring tl case within fifteen days to a relevant court.

17. *Import and Export of Seeds*

1) No person shall import into Ethiopia or export from Ethiopia for sale any prescribed seed unless he is a registered seed importer or a registered seed exporter.

2) No registered seed importer or exorter shall import into Ethiopia or export from Ethiopia any prescribed seed unless all of the following are fulfilled:

(a) such seed is not restricted seed;

(b) such seed conforms to the standards of minimum limits or tolerance levels of germination and purity and maximum limits of moisture content and total and/or objectionable weed seed as may be prescribed;

(c) such seed is labelled and packed in such a container which complies with the provisions of these Regulations;

(d) complies with the provisions of plant quarantine Regulations on importaion of seeds, Council of MInisters Regulation No. 4/1992;

(e) such seed complies with the provisions of Article 4 of these Regulations, and

(f) the name of the variety appears in the Variety List of the country of its origin and is shown on an invoice or delivery note.

3) The Council may exempt the importation of a prescribed seed from conditions stated in sub-Article 2(f) of this Article when it is not possible to receive a certificate from the country of its origin due to the urgency of importing the seeds, or seeds imported into Ethiopia for experiemental purposes or such conditions as may be prescribed by the Council.

18. *Appeal*

1) Any person aggrieved by a decision of the Agency under Articles 4,5,12 and 13, of this Regulation may, within thirty days from the date on which the decision is communicated to him and on payment of such fees as may be prescribed, appeal to the Council or to such authority as may be appointed by the Council to act in his stead.

2) The appellate authority may entertain any appeal after the expiry of the said period of thirty days if it is satisfied that the appeallant was prevented by sufficient cause from filling the appeal on time; the appellate authority shall proceed with the hearing and making decision thereof.

፫· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)መሠረት ይግባኝ ሰሚው ባለሥልጣን ይግባኙ እንደደረሰው አቤቱታውን ሰምቶ በተፋጠነ ሁኔታ ውሳኔ ይሰጣል።

፬· በዚህ አንቀጽ መሠረት በይግባኝ ሰሚ ባለሥልጣን የተሰጠ ማናቸውም ውሳኔ የመጨረሻና ተፈጻሚ ይሆናል።

፲፱· <u>መመሪያ ስለማውጣት</u>

፩· ምክር ቤቱ፤

ሀ) አዲስ ዝርያዎችን፣ የዘር አምራቾችን፣ አስመጪ ዎችን፣አዘጋጆችን፣ የአከፋፋዮች እና የሻጮችን ምዝገባ፣ የዘር ጥራት ቁጥጥርን፣ የዘር ሽያጭን ፣ የዘር ምስክር ወረቀትን፣ የዘር ምርመራን እና ዘር ወደ ሀገር ውስጥ ስለማስገባትና ወደ ውጭ መላክን፣

ለ) የተደነገገ ዘር አምራች፣ አስመጪ ፣ ላኪ፣ አዘጋጅ፣ አከፋፋይና ሻጭ በዚህ ሥራ እንዲሠማራ በድርጅቱ የሚሰጠውን የሥራ ፈቃድ ስለማ ውጣት፣ ስለማሳደስ፣ ፈቃዱ ፀንቶ ስለሚቆይበት ጊዜ፣ ስለሚታደሰበትና ስለሚሠረዝበት ዝርዝር ሁኔታ ፣ እና

ሐ) ሌሎች በደንብ የተካተቱ ጉዳዮችን ለማስፈጸም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

፳· <u>ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ደንቦች</u>

ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረኑ ማናቸውም ደንቦች ይህንን ደንብ በሚመለከት ተፈጻሚነት አይኖራቸውም ።

፳፩· <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ መጋቢት ፩ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

3) On receipt of an appeal under sub-Article (1) of this Article, the appellate authority shall, giving the appellant an opportunity of being heard, dispose the appeal expeditiously.

4) Any decision made by the appellate authority under this Article shall be final and binding.

19. *Issuance of Directives*

1) The council may issue Directives for the proper execution of these Regulations in regard to all matters of the following:

(a) new varieties, seed producers, importers, processors, distributors and sellers, seed quality control, sale of seeds, seed certification, seed tests, and import and export of seeds;

(b) work permit issued by the Agency to prescribed seed producers, importers, exporters, processors, distributors and sellers; getting the work permit, work permit renewal, work permit validity period, renewal and cancellation condition; or

(c) the Council may also issue other directives necessary for the proper execution of these Regulation.

20. *Inapplicable Regulations*

No Regulations shall, in so far as it is in consistent with these Regulations, have force or effect in respect of matters provided for in these Regulations.

21. *Entry Into Force*

These Regulations shall enter into force on the date of its publications in the Federal Negarit Gazetta

*Done at Addis Ababa, this 10th day of March, 1997.*

*MELES ZENAWI*

*PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA*

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE